# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" ኢሳ 48 ÷ 17

God's Love, P. O. Box 6734, L.S. MO 64064
mtizazu@hotmail.com ----- Fax 816 – 246 - 9395

**ሚያዝያ 1994 APRIL 2002**

**"ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ።"** ኢሳ 54 ÷ 13

# አ ር ማ ጌ ዶ ን

## ታላቁ የዘመናት መጨረሻ ጦርነት መድረክ

አንድ ጊዜ ቢሊ ግራም በሬድዮ መልዕክታቸው ሲናገሩ
"በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በአንድ እጅ÷የዜና መጽ
ሔታችንን ደግሞ በሌላ እጃችን ይዘን መገኘት አለብን" ብ
ለዋል። የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ እያነበብን ፍጻሜ
ውን ደግሞ በዜና መከታተል አለብን ለማለት ነው። ይህ ዕ
ውነተኛ አባባል ነው። ያለንበት ዘመን በቸልታ የሚኖርበት
ዘመን አይደለም። ምክንያቱም የአርማጌዶን ውግያ በመባ
ል የሚታወቀው ጦርነት እጅግ ስለተቃረበ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈው ከሚገኙት ትንቢቶች የሚበዙ
ት በየጊዜአቸው ተፈጽመዋል። የተቀሩትም እየተፈጸሙ
ናቸው። ለምሳሌ አይሁድ ከ1451 ዓመተ ዓለም እስከ 70
ዓመተ ምሕረት የራሳቸው ሐገር ነበራቸው። ሆኖም በኦሪት
ዘሌዋውያን 26÷33 የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ በም
ድር ሁሉ ላይ ተበተኑ። ትንቢቱም "እናንተንም በአሕዛብ
መካከል እበትናችኋለሁ÷ሰይፍንም አስመዘዝባችኋለሁ ምድ
ራችሁም የተፈታች ትሆናለች÷ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆ
ናሉ።" የሚል ነው።

ስለ ስደት ዘመናቸውም ፍጻሜ የተነገረውን ትንቢት በሌ
ላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናገኛለን። እንዲህ ይላል።
"በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል÷የቀረውን የሕዝቡን ቅሬታ
ከአሦርና ከግብፅ÷ከጳጥሮስና ከኢትዮጵያ ከኤላምና ከሰናኦ
ር ከሐማትም÷ከባሕርም ደሴቶች ይመልስ ዘንድ ጌታ እንደ
ገና እጁን ይገልጣል። ለሕዝብም ምልክትን ያቆማል÷ከእስ
ራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል÷ከአይሁድም የተበተኑትን
ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል÷የኤፍሬምም ምቀኝነ
ት ይርቃል÷ይሁዳንም የሚያስጨንቁ ይጠፋሉ÷ኤፍሬምም
በይሁዳ አይቀናም÷ይሁዳም ኤፍሬምን አያስጨንቅም።"
(ትንቢተ ኢሳይያስ 11÷11-13) የኸኛውም ትንቢት በ19
48 ዓም እስራኤል ሐገር ከሆነችበት ጀምሮ ተፈጽሞ በመ
ጠናቀቅ ላይ ነው። እስከ ዛሬም ድረስ አይሁድ እንደ ንስር
ክንፍ ባለ መብረር ከአራቱ ማዕዘናተ ዓለም ወደ ቃል ኪዳን
ሐገራቸው እየተከማቹ ናቸው።

በዚሁም አኳያ የዓለም ኃያላን መንግሥታት "የአርማጌ
ዶን ሸለቆ" በሚባል ሥፍራ በመጨረሻው ዘመን ለታላቅ ጦ
ርነት እንደሚከማቹ ተጽፎአል። "… በታላቁም ሁሉን በ
ሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያስከት
ቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።"… "በዕብራ
ይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ሥፍራ አስከተቱአቸው።"
(ዮሐንስ ራዕይ 16÷14 እና 16) ይህም ሁኔታ በዓለም ዜና
እንደምንከታተለው መልክ እየያዘ መጥቶአል።

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ÷የዓለምን መንግሥታት የሚ
ወክሉ የጦር ሠራዊት በፍልስጢኤም ክልል ተከማችተው
ከቆዩ በኋላ በአርማጌዶን እንደሚሠፍሩ ያመለክታል። የአር
ማጌዶን ዘመን (የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት) የታላቁ መ
ከራ ጊዜ ይባላል። በዚህ ክፉ ጊዜ በትንቢት መጻሕፍት
አውሬው እና አመጸኛው የሚባል አንድ ታላቅ ንጉሥ ይነሣ
ል። ይኸውም ሐሰተኛው መሢሕ የሚባለው ነው። መንግ
ሥቱም የአሥር መንግሥታት ጥምር (confederation) ይሆ
ናል። "ያየሃቸውም አሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተ
ቀበሉ አሥር ነገሥታት ናቸው፤ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአ
ንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ፤" (ዮሐንስ
ራዕይ 17÷12)

ይህም መንግሥት በመከራው ዘመን መግብያ ላይ ፍልስ
ጢኤምን (የእስራኤልን አካባቢ) በቁጥጥሩ ሥር ያስገባል።
"ንጉሡም እንደ ፈቃዱ ያደርጋል ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋ
ል÷ በአማልክት ሁሉ ላይ ራሱን ታላቅ ያደርጋል÷በአማልክ
ትም አምላክ ላይ በትዕቢት ይናገራል ቁጣም እስኪፈጸም
ድረስ ይከናወንለታል÷የተወሰነው ይደረጋልና።" (ትንቢተ
ዳንኤል 11÷36)

አመጸኛው ንጉሥ በመከራው ዘመን አጋማሽ ገደማ ይሁ
ዲዎችን በግፍ ለማጥፋት ይነሣሣል። "በልዑልም ላይ ቃል
ን ይናገራል÷ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል÷ ዘመናትንና
ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል ፡ እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት
እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ።" (ትንቢተ ዳንኤል
7÷25) "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን
ትዕዛዝ የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘሯ
የቀሩትን ሊዋጋ ሄዶ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።" "ቅዱሳን
ንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው÷ በነገ
ድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰ
ጠው ።" (ዮሐንስ ራዕይ 12÷17 እና 13÷7)

የዓለም ሕዝቦችም በሐሰተኛው መሢሕና በሐሰተኛው ነ
ቢይ ይታለላሉ። "ይድኑ ዘንድ የዕውነትን ፍቅር ስላልተቀ
በሉ ለሚጠፉ÷የእርሱ መምጣት በተዓምር ሁሉና በምልክቶ
ች በሐሰተኛ ድንቆችም በአመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሴ
ይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት÷በዕውነት ያላመ
ኑ ነገር ግን በዓመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እን
ዲቀበሉ÷ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አ
ሠራር ይልክባቸዋል።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2÷ 9-12)

የሚሳሳተውም የዓለም ሕዝብ እስራኤልን ለማጠፋት ሐሰ
ተኛውን የተባበረዋል። በዚሁም ዘመን በስተመጨረሻ የዓለ
ም ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ከብበው ለማጥፋት የሚያደርጉት
ጥረት ከፍተኛ ይሆናል። (ትንቢተ ዘካሪያስ 14) በኢየሩሳሌ
ም (በአርማጌዶን ሸለቆ) የሚደረገው ይኸው ጦርነት ነው
እንግዲህ የአርማጌዶን ጦርነት የሚባለው። በዚህ ወቅት
መሢሕ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ኃይል ዳግመኛ ይመ
ጣል። (መሢሕ ማለት ረድኤት (ኢየሱስ) ይመጣል ማለት ነው።)

በአሁኑ ወቅት ሩስያ የአረብ ሐገሮችን በማስታጠቅ የመካ
ከለኛውን ምሥራቅ ለታላቅ ጦርነት እያዘጋጀች ነው። የአ
ረቦች እያከረሩ መሄድና የሕዝበ እስራኤል ከተሰደዱባቸው
ሐገሮች መመለስ በቀጠለ መጠን ÷ እስራኤልም ሠፈሮቿን

ባስፋፉች መጠን፥ የሚበረታው የፖለቲካ ግፊት እያደር የአርማጌዶንን ጦርነት እያቀረበው ነው።

የዚህ ዓለም ገዥና ተከታዮቹ የአመጻቸውን የመጨረሻ ኃይል በአርማጌዶን ጦርነት አማካኝነት መግለጻቸው የማይቀር ነው። ይሁን እንጂ የሴይጣን አመጻ ከሰማይ ተሸንፎ እንደተጣለ፥በምድርም በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ሥልጣኑ እንደ ተሻረ፥ለመጨረሻው ይሸነፋል። ሠራዊቱም ሁሉ ይሸነፋሉ። መጽሐፍ እንዲህ ይላል ፦ “ሕዝብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል። እርሱም (ኢየሱስ) በብረት በትር ይገዛቸዋል። እርሱም ሁሉን የሚገዛውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቅያ ይረግጣል።” (የዮሐንስ ራዕይ 19፥15)

እግዚአብሔር የዓለምን መንግሥታት በአርማጌዶን የሚቀጣበት ምክንያት የእርሱን ምርጦች አይሁድን በማንገላታታቸው ብቻ ሳይሆን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመኑት ስላደረጉት አመጻና አለመታዘዝ ነው። “ሕዝብን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ኢዮሳፍጥ ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ፤በዚያም ስለ ሕዝቤና ስለ ርስቴ ስለ እስራኤል በአሕዛብ መካከል የበተኑአቸውን ምድሬንም የተካፈሉትን እፋረድባቸዋለሁ።” “ዓለሙን ስለ ክፋታቸው ክፋዎቹንም ስለ በደላቸው እቀጣለሁ የትዕቢተኞችንም ኩራት እሽራለሁ፥የጨካኞቹንም ኩራት አዋርዳለሁ።” (ትንቢተ ኢዮኤል 3፥2 እና ትንቢተ ኢሳይያስ 13፥11)

የአርማጌዶን ጦርነት ታላቁና የመጨረሻው የጌታ ቁጣ ይሁን እንጂ ከዚያ ቀደም ሲል በርካታ ልዩ ልዩ ፍርዶች ወደ ምድር ይላካሉ። ከእነዚህ ቁጣዎች የምንድንም የማንድንም እንኖራለን። መጽሐፍ እንዲህ ይላል። “በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።” (የዮሐንስ ወንጌል 3፥36) (ከጐስፐል ትራክት ተተረጎመ) (ይህንን መልዕክት ያዘጋጀነው ከሁለት ዓመት በፊት ነበረ። ሆኖም በዚያን ጊዜ ስርጭታችን ባለንበት ከተማ የተወሰነ ነበር። ስለዚህ አሁን በአሕጉር አቀፍ ያሉ አንባቢዎቻችን የቀደሙትን መልዕክቶቻችንን እንዲያነቡ እንደ ገና አቅርበናል)

*******************

# ጻድቅ ሰው

*የደኅንነት ምልክቱ ጻድቆ ከሞት መለየቱ*
*ከኩነኔ ነፃ ወጥቶ በየሱስ መልክ መሠራቱ*
*የእግዚአብሔር ሰው መሆንና ከጻድቃን ጋር መጠራቱ*
*በአዋጅ መልክ ሳይነገር ሳይመታ ነጋሪቱ*
*በጌታ ፊት እንደሚታይ የቅዱስ ሰው ምልክቱ*
*እንዴት ይሆን የሚታወቅ አበክሮ ሐቁ ዕውነቱ?*

*ብዙ ጠልቆ የተማረ ሥነ መለኮት ያወቀ*
*አሳምሮ የሚቀድስ በስብከትም የረቀቀ*
*ከደብር አድባር በመዞር ጸሎት ማኪያሂድ የሚወድ*
*አጋንንትን በጌታ ስም ተግቶ ከሰው የሚያስወግድ*
*በመጠንቀቅ እጅግ ብርቱ አስተዋይ ነው የተባለ*
*አለቅነቱን ሲጠብቅ እንደ እርሱ ንቁ የሌለ*
*በጌታ ፊት እንደሚታይ የጻድቅ ሰው ምልክቱ*
*በዚህ ይሆን የሚታወቅ ባሕሪይና ልዩነቱ?*

*ሙሴም፥ካሕንም፥ደብተራም፥አቡን ኤድስ ቆዶሱ*
*የወገኖቹም አለቃ ፥ ሕጉም ዳኛውም እርሱ*
*ሁሉ ሊሳሳት ሲችል እርሱ ግን የሁሉ አራሚ*
*በደለኞች ሲናዘዙ፥የተጣሉት ሲታረቁ፥እርሱ ግን “በጽድቁ” ቋሚ*
*የእግዚአብሔር ሰው የሚባለው በጌታ ፊት ተመርምሮ*
*እንዲህ ዓይነቱ ሰው ይሆን ምሥጉንና ባለ አእምሮ?*

*በውነት ጻድቅ የትኛው ነው በጌታ ፊት የሚደነቅ?*
*በትምሕርቱ በኢየሱስ ቃል ተመዝኖ የማይናቅ*
*የእኛ ዘመን የአምላክ ሰዎች በምሳሌ የሚያወሱት*
*የዛሬም ዘመን ወጣቶች ለልጅ ልጆች የሚነግሩት*
*ከምዕተ ዓመት በኋላ በመጻሕፍት የሚያነቡት*
*አበው በክብር በአድናቆት በጉባኤዎች የሚጠቅሱት*
*የእግዚአብሔር ሰው መሆንና ከጻድቃን ጋር መጠራቱ*
*የኸ ነው ወይ ፤ ወይስ ሌላ ፤ መታወቅያ ልዩነቱ?*

*መላኩ ትዕዛዙ*

*******************

# “ከማትሪክ” በኋላ

*በሐገራችን አሥራ ሁለተኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ማትሪክ ተፈትነው እንደሚመረቁት በሌሎችም ሐገሮች እንዲሁ ይደረጋል። በአንድ የምዕራብ ሐገር አንድ የሐብታም ቤተሰብ ልጅ ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል መመረቅያው ጊዜ ደረሰ። በዚያም የሐብታሞች መንደር ልጅ ሁሉ ሲመረቅ መኪና መሸለም የተለመደ ነበር። ይህም ልጅ ከአባቱ ጋር ሆነው የሚስማማውን መኪና ሲፈልጉና ሲያማርጡ ወራት አሳለፉ። ለምረቃውም ሳምንት ሲቀረው የተወደደ መኪና ተገኘ ልጁም በምረቃው ዕለት ይህ ያገኙት መኪና እንደሚሰጠው ርግጠኛ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ።*

*ሳምንትም አለፈ። የምረቃውም ቀን ደረሰ። ልክ ከሥርዓተ ምረቃው በኋላ አባትየው አንድ በስጦታ መጠቅለያ የተጠቀለለ ነገር አምጥቶ ለልጁ ሰጠው። ልጁም ገና ለገና የመኪና ቁልፍ አለመሆኑን ሲያውቅ ፊቱ ተጨማደደ። እያዘነ ገለጥ ሲያደርገው መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። ምን በድየዋለሁ በማለት በአባቱ እጅግ አዘነ። ልቡ ተሰበረ። መጽሐፍ ቅዱሱንም ወደ መሬት ወረወረና የአባቱን ቤት ትቶ ሄደ። ከአባቱም ጋር ሁለተኛ አልተያዩም።*

*ከረዥም ዓመታት በኋላ የአባቱን ሞት መርዶ በሰማ ጊዜ መቼም አባት ነውና ወደ ቤቱ ተመለሰ። ሐዘኑንም ከተወጣ በኋላ አንድ ቀን የእርሱ ውርስ የሚሆኑትን የአባቱን ዕቃዎች ያገላብጥና ይመለከት ነበር። በዚህም ጊዜ አባቱ በምረቃው ዕለት የሰጠውን መጽሐፍ ቅዱስ አገኘ። መጽሐፍ ቅዱሱንም የሸፈነውን ትብያ ጠረግ ጠረግ አደርጎ ገለጥ ሲያደርገው ለማመን የሚያስቸግር ነገር ዓይኑ ፊት ከች አለበት። ይኸውም ለምረቃው ስጦታ የተመረጠው መኪና ዋጋ በሙሉ የተጻፈበት ቼክ ነው። ቼኩም የተጻፈው በምረቃው ዕለት ነበር።(Chicken soup ከሚል መጽሐፍ ተወስዶ የተተረጐመ) የሚያስፈልግህን ሁሉ በውስጡ አድርጎ እግዚአብሔር አባትህ የሰጠህን መጽሐፍ ቅዱስ ገልጠህ ታነባለህ ? አዎን ካልህ ፥ ምን ያክል ? አንቺስ? “አንተን እንዳል በድል ፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ (አጥንቼ ተረዳሁ)።” (መዝ 119፥11)መጽሐፍ ቅዱስ ሳይረዱ እግዚአብሔርን ማወቅ፥ሳያውቁስ ማመን እንዴት ይቻላል?*

*ኢየሱስ ጌታ ነው። ጌታ ይባርክህ።*